www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ሃይማኖት



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀደምትነት ከታወቁ የዓለም አቢያተ ክርስቲያናት አንዷ እንደሆነች ግልጽ ነው።

ቤተክርስቲያኒቱ የተቋቋመችበ ትን ዘመን ከእውነተኛ የታሪክ ገጽታ ስናስተያየው፣ ምንም እንኳን በነገሥ ታተ አኵስም በአብርሃ ወአጽብሐ ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን ያስፋፋች መሆኑ ቢታወቅም፣ የተመሠረተችው ግን በ፴፬ ዓ.ም ነው። የሐ.ሥ.፰፡፳፮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በጃንደረባው ሐዋርያነት በአኵስም ከተማ ከተቋቋመች ጀምሮ እስከ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመን ድረስ ግልጽ የሆነ መለያ አላስቀመጠችም ነበር።

በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ዘመነ ጵጵስና እና በአብርሐ ወአጽብሃ ዘመነ መንግሥት ግን ሕዝባውያኑና ካህናቱ፣ ሊቃውንቱና መኳንንቱ፣ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖችና ነገሥታቱ የሚያምኑት እምነት «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት» ተብሎ እንዲጠራ ሆነ።

ይህ ስያሜ በመላ ኢትዮጵያ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የእምነታቸው መለያና የክርስትናቸው መጠሪያ ሆኖ እስከ አሁን ድረስም ያገለግላል።

«ኦርቶዶክስ» የሚለው ቃል የጽርዕ ቃል ሲሆን ትርጉሙ የቀናርቱዕ እምነት የሚል ትርጉም ይኑረው እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሌሎች የተለየችበትን አቋም ለይቶ አያሳይም።

«ተዋሕዶ» የሚለው ቃል ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ የተመሠረተችበትን እምነት ወይም ሃይማኖት ስምን ከምግባር አስተባብሮ ይዞ በመገኘቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ መለያ አድርጋ ትጠራበት አለች።

ይህ ስያሜ እንደ አጋጣሚ የተገኘ ነገር አልነበረም። ነገር ግን ንጽሕናን

## ትምህርተ ተዋሕዶ

ከመም.ዕንቁባሕርይ ተከስተ

ከቅድስና፣ ሊቅነትን ከመንፈሳዊነት ጋር አሟልተው በያዙ ሙሉ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር በሰጡ፣ በእምነትና በትምህርት በበሰሉ፣ በሀገር ሊቃውንት ድካምና ጥረት የተገኘ ነው እንጂ።

### ትምህርተ ተዋሕዶ

### (አንቀጸ ተዋሕዶ)

የተዋሕዶ ትምህርት «አንቀጸ ተዋሕዶ» ይባላል። ምሥጢረ ተዋሕዶ ሊገኝ የቻለው «ተወሐደ» አንድ ሆነ ካለው አንቀጽ የወጣ፣ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶን የሚያስረዳ ስለሆነ ነው። (ሃይማኖተ አበው ፊልክስዮስ ሰማዕት ክፍል ፪) ተመልከት።

ይህም የልደታቱን መነሻ ሲያዩ ጥቅስ «ከመዝ ነአምን ዘአልቦቱ እም በሰማያት ወአብ በዲበ ምድር፣ በሰማይ ያለእናት ከአብ መወለዱን፣ በምድርም ያለ አባት ከድንግል ማርያም መወለዱን እናምናለን» ተብሎ መግለጫ የተሰጠበት ወይም ባሕርያተ ልደታትን በመገንዘብ «ነአምን ክልኤተ ልደታተ» ተብሎ እንዲታመንበት ያስቻለ፣ ምሥጢር መሆኑ ይታወሳል። ለዚህም ቅዱስ ባስልዮስ በሰፊው አብራርቶታል።

«ይደልወነ ንእመን ከመ ቦቱ ለወልደ እግዚአብሔር ክልኤቱ ልደታት ቀዳማዊ ልደቱ እም እግዚአብሔር አብ እምቅድመ ኵሉ መዋዕል፣ ወዳግማዊ ልደቱ እም እግዚእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም በደኃሪ መዋዕል።»

ለወልደ እግዚአብሔር ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምን ዘንድ ይገባናል፣ አንዱ ከዘመን ሁሉ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው ልደት ነው። ሁለተኛውም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በኋላ ዘመን የተወለደው ልደት ነው። (መዝ. ፪፥፯።፩፻፲(፩፻፱) ቁጥር ፫። ማቴ. ፲፱፥፳፰። ዮሐ.፲፮፥፳፰ እና ፳፰። ገላ.፬፥፬። ሃይማኖተ አበው ምዕ.፴፬ ቁጥር ፮ ክፍል ፫ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ምዕ.፴፫፥ ክፍል ፪ ቁጥር ፲፯፥፲፰።)

የተዋሕዶ ይዞታ ከሁለት ባሕርያተ ልደታት ምንጭነት፣ አንዱን የአማኑኤልን ህላዌ ቅውም አድርጎ ሲያስገነዝብ ጥቅስ ቄርሎስ «ኢትፍልጥ ሊተ እምድኅረ ትድምርት እስመ ዘፈለጠ እንተ ባሕቲቶ ብእሲ ወእንተ ባሕቲቶ አምላከ ቃለ ክልዔተ ይረስዩ ለአማኑኤል፤ ከተዋሕዶ በኋላ አትለይብኝ፣ ከተዋሕዶ በኋላ

www.ethiopianorthodox.org

ብቻውን ሰው፣ ብቻውን አምላክ ቃል የሚል ሰው ቢኖር፣ አማኑኤልን ሁለት ያደርገዋል።» ብሎአል።

ባስልዮስ ዘእንጾኪያም፣ «ኢይት ከፈል ኀበ ክልዔቱ ህላዌያት እም ድኅረ ተዋሕዶ እስመ ለምንታዌ አእተታ ተዋሕዶ፣ ወተዋሕዶኒ ያግኀሥ ኩነኔሁ ለምንታዊ እስመ ውእቱ ተዋሕዶ አካላዊ ዘኢትከፈል ከተዋሕዶ በኋላ ወደ ሁለት ባሕርይ አይከፈልም፣ ተዋሕዶ ሁለትነትን አስወግዶአልና፣ የሁለትነትንም ፍርድ አርቆአል። እርሱ የማይከፈል አካላዊ ተዋሕዶ ሆኖአል» ብሎአል። (ሃይማኖተ አበው ዘባስልዮስ ምዕ.፺፯ ቁጥር ፲፯ ክፍል ፩)

ቅዱስ አትናቴዎስም «አኮ ዘንብል እስመዘንቱ ወልድ ክልኤ ህላዌ ለአሐዱ ዘንሰግድ ወለካልኡ ዘኢንሰግድ አላ አሐዱ ህላዌ ውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰገወ። ንሰግድ ሎቱ ምስለ ሥጋሁ አሐተ ስግደተ።

ይህ ወልድ ለአንዱ የምንሰግ ድለት ለአንዱ የማንሰግድለት ሁለት ባሕርይ ነው፣ የምንል አይደለም፣ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ባሕርይ አንድ ነው እንጂ፣ ከሥጋው ጋር አንዲት ስግደትን እንሰግ ድለታለን እንጂ ብሎአል። (ሃይማ ኖተ አበው ዘአትናቴዎስ ምዕ.፳፯ ቁጥር ፲፰ ክፍል ፲፫።)

ቅዱስ አቡሊድስም «ወኢንከ ፍሎ ለሰማያዊ እምነ ምድራዊ ወኢለ ምድራዊ እምሰማያዊ እስመ ክፍላትሰ ዐመፃ ውእቱ ወኢነሀቦሙ ለእለ ይብሉ ክልኤ ህላዌ ምክንያተ ለፍ ልጠት» ሰማያዊ መለኮትን ከምድ ራዊ ሥጋ፣ ምድራዊ ሥጋንም ከሰማ ያዊ መለኮት አንለየውም፣ መክፈል ክሕደት ነውና፤ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ለሚሉ ሰዎች ለመለየት ምክንያት አንስጣ ቸው።» (ሃይማኖተ አበው ዘአቡሊድስ ምዕ.፴፱ ቁጥር ፳።)

እኛ ግን መለየት፣ ሕፀት መቀላ ቀል ሳይኖርበት አንድ ሆነ እንላለን፣ ከተዋሕዶ በኋላም ወደ ሁለትነት አይከፈልም እንላለን (ዮሐ.፫፥፲፰። ፩ቆሮ.፰፥፮ ሃይማኖተ አበው ዘቴዎ ዶጦስ ምዕ.፺፫ ቁጥር ፴፩ ክፍል ፫።)

በምሥጢረ ሥጋዌ (በተዋሕዶ) ትምህርት ከትስብእትና ከተዋሕዶ በፊት ስለ ነበረው አቋም በአንቀጽ ተከፍሎ ሊነገር ሲገባ፣ ከትስብእትና ከተዋሕዶ ወዲህ ስላለው ምሥጢር ግን በአንቀጸ ተዋሕዶ መነገር እንዳለበት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሁሉም የሚስማሙበት ነው።

ስለዚህም ዮሐንስ አፈወርቅ «ወአሠረ ክልዔቱ ህላዌያት በበይና ቲሆሙ በተዋሕዶ «ሁለቱን እየራስ የሆኑትን ህላዊያት በተዋልዶ አንድ አደረገ» ይላል። (ሃ.አ.ገጽ.፪፲0፵፱) ክፍል ፳፪ ቁጥር ፳፪።

ሳዊሮስ ዘአንጾኪያም «ኢይት ክሐል ይፍልስ ሥጋ ዘይትዌለጥ ኀበ ዘኢትዌለጥ ወበ ከመ ግብር ዘይከውን እምክልዔቱ ህላዌያት ሶበ የኀብሩ በበይናቲሆሙ ይከውኑ አሐደ እንዘ አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ እምኅላዌሁ እንዘ ቀዳሚ ክልዔቱ።

## ትርጉም

የሚለወጥ ሥጋ የማይለወጥ ባሕርይ ወደ መሆን ይለወጥ ዘንድ አይቻልም፤ ከሁለት ባሕርያት እንደሚገኝ ሥራ፤ ጥንቱን ሁለት ሲሆኑ አንዱም አንዱ ከባሕርዩ ሳይለወጥ እርስ በእርሳቸው በተዋሕዶ ጊዜ አንድ ይሆናሉ።» ብሏል።

ሃይ.አበው ገጽ ፫፻፸፰ ክፍል ፰ ቁጥር ፴

ተዐቅቦ ማለት – አለ መለወጥ፣ አለመቀላቀል፣ አለመጣፋት አለመደባለቅ፣ ነው ከትንሣኤሙታን እንደ ነፍስና በኋላ ሥጋ ተዋሕዶ ነው።

ቅዱስ አትናቴዎስም ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ በተናገረበት አንቀጽ እንደሚከተለው ይገልጻል።

«ወኪያሁ ለቢሶ ቃለ እግዚአብሔር ሥጋ ኮነ እንዘ ኢይትዌለጥ እምህላዌ መለኮቱ ወለውእቱሂ ሥጋ ዘለብሶ ረስዮ ዕሩየ ምስሌሁ በአሐዱ ህላዌ እንዘ ኢይትዌለጥ እምህላዌ ሰብእናሁ።

የእግዚአብሔር ቃል ከባሕርየ መለኮቱ ሳይለወጥ እርሱን ተዋሕዶ ሰው ሆነ፣ የተዋሐደውን ያንን ሥጋም ከሰውነቱ ባሕርይ ሳይለወጥ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ፣ በመሆን ከእርሱ ጋር አንድ አደረገው (ሃይማኖተ አበው ዘአትናቴዎስ ምዕ.፴ ቁጥር ፯።)

ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ዘእግ ዚናዙም

«ወኢፈለሰ ህላዌ መለኮቱ ኀበ ህላዌ ትስብእቱ ወኢህላዌ ትስብእቱ ኀበ ህላዌ መለኮቱ አላ በአሐዱ አካል ወለደቶ እግዚዕትነ ማርያም ድንግል ወበአሐዱ ህላዌ ሰገዱ ሎቱ ሰብአ ሰገል።

## ትርጉም

የመለኮቱ ባሕርይ ወደ ሰውነቱ ባሕርይ አልተለወጠም የሰውነቱ ባሕርዩም ወደ መለኮቱ ባሕርይ አልተለወጠም፣ ድንግል ማርያም አንድ አካል ሆኖ ወለደችው እንጂ፤ ሰብአ ሰገልም አንዱ ባሕርይ ሆኖ ሰገዱለት እንጂ (ማቴ.፩፥፲፰–፳፫ ምዕ.፪፥፩–፲፪። ሃይማኖተ አበው ዘጎርጎርዮስ ምዕ.፰ ቁጥር ፲፯ ክፍል ፩)

የኮነንና የኀደረን አብነት (ትርጉም)

«ቃል ሥጋ ኮነ፣ ቃል ሥጋ ሆነ» «ወኀደረ ላዕሌነ፣ በእኛም አደረ» በሚል በቅዱስ መጽሐፍ አባባል የተዋሕዶ ምሥጢር መመሥረቱ ይታወቃል። ዮሐ.፩፥፲፬። «ኮነና፣ ኀደረ» ሆነ፣ አደረ (እነዚህ ሁለቱ የተዋሕዶውን አንቀጽና የተአቅቦን ምሥጢር በመያዝ፣ እንደ አለቃና እንደ ጠበቃ ሆነው ይጠባበቃሉ። በ«ኮነ» የተነሱት መናፍቃን

www.ethiopianorthodox.org

በ«ኅደረ»፤ በኅደረ «የተነሡት መና ፍቃን በ«ኮነ» ይረታሉ» ኮነ፣ ኅደረ» እንደ አለቃና እንደ ጠበቃ ይጠባ በቃሉ እንጂ፣ አንዱ ከሁለተኛው ተነጥሎ! ተለይቶ! «ኮነ» ለብቻው፣ ኅደረም» ለብቻው፣ በመነጣጠል የተዋሕዶን ምሥጢር ጠንቅቆ ለመጠበቅ፣ አያስችሉም። ይህ የኢት ዮጵያ ሊቃውንት የብሂላዊ ትርጓሜ አብነታዊ አዋጅ ነው።

የእነዚህም ትንትና ለመርዳት የሚከተለውን ይመለከቷል።

ለምሳሌ ንስጥሮስ «ኮነን» «የኅደረን» ንባብ ይዞ ምሥጢሩን ሳይመረመር በአንድ ክርስቶስ ሁለት ህላዌያት አሉ» ብሎ በመተርጐም ውስጣዊ መለያየትን፣ መፈራረቅን (ቡዓዴንና ፍልጠትን) በምሥጢረ ተዋሕዶ አመጣ። ለዚህም «የኮነን» እውነተኛ ትርጉም ወይም ፍቺ የያዘ ከኅደረ ጋር የሚያገናኝ (የሚያስማማ) ተዐቅቦ እንዲኖር አስፈለገ እነሆም» ዘእንበለ ቡዓዴ፣ ዘእንበለ ፍልጠት፣ በኢተላፅቆ ያለ መለየት፣ ያለ መከፈል፣ ያለመነባበር (አነባብሮ) የሚሉ ቃላት የ«ኮነ»ን ምሥጢር ይዘው «ኅደረ» ያለውን አንቀጽ እንዲጠብቁ ተደርጐ የሥግው ቃል በተዋሕዶ ተጠናቀቀ።

አውጣኪ በአንዱ ሥግው ቃል (ክርስቶስ) ቱስሕተ (መደባለቅ) (ውላጤ የሰውነት መለወጥ) ሚጠት (መለዋወጥ) እንዳለበት፣ ሰውነቱ ወደ አምላክነቱ እንደ ተለወጠ ተናገረ።

አውጣኪ «ኅደረን» በመተው የ«ኮነን» ንፍቺ በተሳሳተ አተረጓጐም «ኮነን» ተለወጠ» በሚል ቃል ተርጉሞ ተሰናከለበት ( «እንደ እሱ ሐሳብ ወይም አተረጓጐም ቢሆን ኖሮ ምሥጢረ ተዋሕዶን ደመሰሰበት።

ለዚህም ጠንቀኛ ትርጉም መጠበቂያ (ልጓም) አስፈለገ። እነሆም «ዘእንበለ ቱስሕት ዘእንበለ ውላጤ፣ ዘእንበለ ሚጠት ያለመደበላለቅ፣ ያለመለወጥ ያለመለዋወጥ ያለመ መላለስ» የሚሉ ቃላት። የኅደረን ምሥጢር ይዘው የኮነን ፍቺ ወደሌላ እንዳይሄድ ይኸውም በመለወጥ እንዳይተረጐም ይጠብቁ ዘንድ ተደረገ።

ስለአንቀጸ ተአቅቦ መጻሕፍት ጠንቅቀው ያስረዳሉ። ለዚህም

አቡሊድስ እንደ ገለጸው «ወዓዲንብል አልቦቱ ቱሳሔ ወኢካልዕ ነገር ዘከመዝ ወኢይተልዎ ንባበ ቱሰሔ በእንተ ነገረ ተዋሕዶ ወልድ ወልደ እግዚአብሔር ተሰነአወ ወኮነ ሰብአ ወበአንተ ዝንቱሂ ነገር ኢይበው ቱሳሔ ውስቴቱ ዘከመ የእምኔ አልክቱ ወኢተወለጠ ህላዌ ቃል ኀበ ህላዌ ትስብአት ወህላዌ ትሰብእት ኀበ ህላዌ ቃል ጸዕሙ ይሄልው ክልኤቱ ህላዌያት በበዓላዌሆሙ እንበለ ውላጤ።

ዳግመኛም መቀላቀል ይህንንም የመሰለ ሌላ ነገር የለበትም እንላለን ተዋሕዶው እውነተኛ ስለሆነ ተቀላቀለ ማለት አይስማማውምና። የእግዚአብሔር ልጅ ወልድ ዋሕድ ነፍስን ሥጋን ነስቶ ሰው ሆነ ባልን ጊዜም ስለዚህም ነገር ቢሆን እነዚያ እንደሚያምኑ መቀላቀል የለበትም፣ የቃል ባሕርይ የሥጋን ባሕርይ ወደመሆን፣ የሥጋ ባሕርይም የቃልን ባሕርይ ወደመሆን አልተለወጠም፣ ሁለቱ ባሕርያት ያለ መለዋወጥ፣ ባለመቀላቀል ጸንተው ይኖራሉ እንጂ (ዮሐ.ምዕ.፩ ቁጥር ፩–፲፰። ፫፥፲፰ ፩ቆሮ.፰፥፮።) ሃይማኖተ አበው ዘአቡሊድስ ምዕ.፵፫ ቁጥር ፳–፮ ክፍል ፩።

በዚህም ተዐቅቦ የሥግው ቃል ተዋሕዶ ተጠነቀቀ፣ ታወቀ። ይህ ተዐቅቦ ባይኖር የአውጣኪን ግንጥል ሐሳብ ለተከተለ ሰው የተዋሕዶ እምነቱንና በቅዱሳት መጻሕፍት ያለው የአተረጓጐሙን መንገድ ያቃውሰበት ነበር።

መናፍቃን «ኮነ» ያለውን ይዘው «በትረ ሙሴ ኮነት ዓርዌ ምድር» የሙሴ ብትር ዓርዌ ምድር እባብ ሆነች» ዘጸ.፬ ቁጥር ፫።

«ብእሲተ ሎጥ ኮነት ሐወልተ ጼው ማለት የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት ሆነች» ዘፍ. ምዕ.፲፱ ቁጥር ፳፮) የሚለውን ገጸ ንባብ ይዘው ምሥጢሩን ሳይመረምሩ መለኮቱ ተለውጦ ሥጋ ሆነ ብለው ለተነሱ መልሱ «ኅደረ» አለባችሁ «ኅደረ» ብለው ለተነሱ መናፍቃን ደግሞ «ኮነ» አለባችሁ በማለት በኅደረ «የተነሱ መናፍቃን በ«ኮነ» በ«ኮነ» የተነሱ መናፍቃን በ«ኅደረ» ይረታሉ።

ማስጠንቀቂያ «ወበከመ ኅደርኩ ምስለ ሙሴ ከማሁ ኅደርኩ ምስሌከ ማለት ከሙሴ ጋር እንደ ሆንኩ እንዲሁ ከአንተ ጋር መሆኔን፣ እንዳለው አይደለም) ኢያሱ ምዕ.፫ ቁጥር ፯።

እግዚአብሔር በነቢያት፣ በሐዋር. ያት፣ በሊቃውንት፣ በቅዱሳን እንደ ሚያድር በሥጋ ማርያም አደረ አይባልም።

«ወኢኅደረ ውስቴቱ ዘከመ ኵሉ ሰብ አላ ለሊሁ ነሥአ ሥጋ ሎቱ ለባሕቲቱ ወአስተዓመሮ በተዋሕዶ። አኮ ከመ ኵሎሙ ነቢያት ዘሰፍሐ ቦሙ ወተናገረ ውስቴቶሙ አላ ኮነ ሰብአ ፍጹመ ቃል ሥጋ ኮነ ወኢተ ወለጠ ኢያፍላሰ መለኮቶ ኀበ ከዊነ ትስብእት፣ ወረሰየ ፍጻሜሁ ቅድስተ በብርሃን ምስለ መለኮት»

በሰው ሁሉ እንደሚያድርም አላደረበትም፣ እርሱ ሥጋን ነስቶ ለእርሱ ለብቻው ገንዘብ አደረገው እንጂ። አድሮ እንደ ተናገረባቸው እንደ ነቢያት ሁሉ አይደለም። ፍፁም ሰው ሆነ እንጂ ቃል ሥጋ ሆነ አልተለወጠም፣ መለኮቱን ሰው ወደ መሆን አልለወጠውም። ከመለኮት ጋር ጽኑዕ አንድነቱን በተዋሕዶ አደረገ እንጂ። (ሃይማኖተ አበው ዘኢጲፋንዮስ ምዕ.፶፯ ቁጥር ፳፮–፳፰።

በዚህም «ቃል ሥጋ ኮነ» ቃልም ሥጋ ኾነ አለ እንጂ ኅደረ በሥጋ አላለም። የመለኮትና የትስብእትን ተዋሕዶ የሚያስረዳ የነፍስ የሥጋ ተዋሕዶ ባይኖር ኖሮ በየጊዜው እንደ አሸን የሚፈሉ መናፍቃን ሰውን ሁሉ እያሳቱ በክህደት ማዕበል ባናወጡት ነበር። ✣



2nd year, Number 2, Meskerem 1992